የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሳስ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23[rd] Year, No. 6
ADDIS ABABA, 12[th] December, 2016

**ማውጫ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፬/፪ሺ፱ ዓ.ም

የሥራ ፈቃድ፣ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ እና የሥራ ውል ማፅደቂያ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ…………………ገጽ ፱ሺ፬፻፴፪
ሰንጠረዥ……………………………………....ገጽ ፱ሺ፬፻፴፬

**CONTENT**

Council of Ministers Regulation No.394 /2016

Rate of Fee for Work Permit, Private Employment Agency License and Approval of Contract of Employment Council of Ministers Regulation……………………………………page 9432
Schedule……………………………………. page 9434

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፬/፪ሺ፱

## የሥራ ፈቃድ፣ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ እና የሥራ ውል ማፅደቂያ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያዎችን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭፣ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፺፭ አንቀጽ ፩፻፸፬(፬)፣ በኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ አንቀጽ ፲፯(፩) እና በኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፯ አንቀጽ ፸፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ “የሥራ ፈቃድ፣ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ እና የሥራ ውል ማፅደቂያ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፬/፪ሺ፱” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.394/2016

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE DETERMINATION OF FEES FOR WORK PERMIT, PRIVATE EMPLOYMENT AGENCY LICENSE AND APPROVAL OF CONTRACT OF EMPLOYMENT

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015, Article 174(4) of the Labour Proclamation No. 377/2003, Article 17(1) of the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No.648/2009 and Article 75(1) of the Ethiopia’s Overseas Employment Proclamation No. 923/2016.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the “Rate of Fee for Work Permit, Private Employment Agency License and Approval of Contract of Employment Council of Ministers Regulation No.394/2016”.

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ "የሥራ ፈቃድ" ማለት አንድ የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥሮ ለመሥራት እንዲችል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፺፮ አንቀጽ ፻፸፬(፬) መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፪/ "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ ነው፤

፫/ በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**፫. <u>ስለ አገልግሎት ክፍያ</u>**

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፺፮ አንቀጽ ፻፸፬(፬)፣ በኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ አንቀጽ ፲፩፣፳፭ እና ፴፫ (፫) በተደነገገው መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ በተመለከተው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፡፡

**፬. <u>የተሻረ ሕግ</u>**

የሥራ ፈቃድ እና የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፈቃድ ክፍያዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፪/፪ሺ፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፭. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**2. <u>Definition</u>**

In this Regulation:

1/ “work permit” means a permit issued to a foreign national pursuant to Article 174(4) of the Labour Proclamation No.337/2003 to work in Ethiopia as an employee;

2/ “Proclamation” means the Ethiopia’s Overseas Employment Proclamation No. 923/2016;

3/ definitions provided under the Proclamation shall be applicable.

**3. <u>Service Fees</u>**

Service fees shall be payable for services rendered by the Ministry of Labour and Social Affairs in Accordance with Article 174(4) of the Labour Proclamation No. 377/2003 and Articles 11, 25 and 33(3) of the Ethiopia’s Overseas Employment Proclamation No.923/2016 at the rate prescribed in the schedule attached herewith.

**4. <u>Repeal Law</u>**

The Work Permit and Private Employment Agency License Fees Council of Ministers Regulation No. 282/2013 is hereby repealed.

**5. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of December 2016.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## የአገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ ፈቃድ | ዕድሳት | ምትክ ፈቃድ |
| 1 | የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ | 2000 | 1500 | 1200 |
| 2 | የውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ | 3300 | 3000 | 2700 |
| 3 | የአገር ውስጥ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ | 650 | 550 | 450 |
| 4 | የሥራ ውል ማጽደቂያ | 500 | | |



## SCHEDULE OF FEES

| No. | Types of Services | Amount of Fee (Birr) | | |
|---|---|---|---|---|
| | | For New License | For Renewal of License | For Replacement of License |
| 1. | Issuance of Work Permit for Foreigners | 2000 | 1500 | 1200 |
| 2. | Issuance of Overseas Private Employment Agency License | 3300 | 3000 | 2700 |
| 3. | Issuance of Local Private Employment Agency License | 650 | 550 | 450 |
| 4. | Approval of Contract of Employment | 500 | | |